ከኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የመንገድና የድልድይ ጥገና ተግዳሮቶች

**ክፍል ሁለት**

የመንገድም ሆነ የድልድይ ጥገና ሥራ በአገራችን አዲስ ባይሆንም በጥራትና በወቅቱ የመጠገኑ ጉዳይ ግን እንኳንስ በባለሙያዎች በተጠቃሚው ሕዝብ ዘንድ ሳይቀር ሁሌም እንደ አዲስ የሚነሳ የመነጋገሪያ ርዕስ ነው።

በጥራት ለመጠገን የሚያስችሉ ግብዓቶችን የሚያሳዩ የማንዋል፣ የመመሪያና የስፔስፊኬሽን ችግር የለብንም፤ ከበቂ በላይ የሆኑ በየጊዜው የሚከለሱና በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የሚነገሩ ዕውቀትን የሚያስጨብጡ መጽሐፍት ይገኛሉ። በተጨማሪም የአጭርና የረዥም ጊዜ ስልጠና በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ የወሰዱ ባለሙያዎችም በርካታ ናቸው። ነገር ግን ዕውቀትን ወደ መሬት ለማውረድ የሚችሉና ፍላጎቱ ያላቸው እንዲሁም በጥገና ሥራ ላይ የሰለጠኑ በጥገና ሥራ ትኩረት (ስፔሻላይዝ) በማድረግ የሥራው ባለቤት የሆኑ ባለሙያዎች እጥረት አለ።

ለምሳሌ የአስፋልት መንገዶች በተገነቡ ከዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሲሰነጠቁ ወይም ቅርፃቸውን በመለወጥ ሲሸበሸቡ ወይም ደግሞ በድልድዮች አካል ላይ መሰንጠቅ ወይም የመሸርሸር ምልክቶች ሲታዩ ከንድፈ ሀሳብና ከጠቅላላ ዕውቀት በዘለለ የችግሮቹን ምክንያቶች በግልጽ ለይተው የሚያስቀምጡና ተግባራዊ መፍትሔ በልበ ሙሉነት የሚሰጡ በልምድ የበሰሉ ባለሙያዎች ቁጥር አናሳ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የመንገድም ሆነ የጥገና ሥራው በጥራት ከማይካሄድባቸው ምክንያቶች አንዱ በጥገና ሥራ ትኩረት (ስፔሻላይዝድ) ያደረጉ ሥራ ተቋራጮች አለመኖራቸው ነው።

አብዛኛው ባለሙያ ሁለገብ በመሆኑ ለመንገድና ለድልድዮች ብልሽት ምክንያት ይሆናል ብሎ የሚያቀርበው የቴክኒክ ምክር እንዲሁ ሁለገብ ይሆናል። ወደ ሥራው የሚገቡት ሥራ ተቋራጮችም ሆነ አማካሪ መሐንዲስ ሁለገብ የሆነ እውቀትና ልምድ ይዘው ስለሚገቡ ለሥራው የሚሰማሩት መሣሪያዎችም ሁለገብ እንጂ የጥገና ሥራን በተገቢው የሚከውኑና የመንገድ ብልሽትን ሊያክሙና ሊፈውስ ለዚሁ ሥራ የተፈበረኩ ባለመሆኑ ውጤቱም



ጊዜያዊ እንጂ ዘለቄታዊ አይሆንም።

ስለዚህ የጊዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ ብክነት ከመደበኛ የሥራ ሂደት ጎን ለጎን የሚሄድ መደበኛ ችግር ሆኖ ይታያል። ይህን አገላለፅ በምሳሌ ለማስረዳት አመቺ የሚሆነው በጤናው ዘርፍ ያለው የባለሙያዎች ስብጥር ነው። ማንኛውም ሐኪም የጠቅላላ ሕክምና ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ሁለገብ ሐኪም ሆኖ እንደሚሠራ ይታወቃል። ነገር ግን እንደየዝንባሌውና እንደየችሎታው የልዩ ልዩ ሕክምናዎች ልዩ ባለሙያ ለመሆን ስፔሻላይዝ በማድረግ የኩላሊት፣ የነርቭ፣ የውስጥ ደዌ፣ ወዘተ እየተባለ ትኩረትና ጥልቀት ያለው የሙያው ባለቤት ይሆናል። ነገር ግን በአገራችን በመንገድ ሴክተሩ በዲዛይን ወይም በግንባታው መስክ በጠቅላላ የምህንድስና እውቀት ከመሳተፍ በዘለለ በጠባብና በጠለቀ ሙያ ላይ ትኩረት የማድረግ ዝንባሌ አናሳ ነው።

ለዚህም በዋነኝነት ወደዚህ ስፔሻላይዜሽን ብዙዎችን የሚጋብዝ ተግባራዊ የመስክ ሥራ በብዛት አለመኖሩ እንደምክንያት የሚጠቀስ ሲሆን በአካዳሚክ ደረጃ ግን እስከ ሦስተኛ ዲግሪ ይሰጣል። ይሁን እንጂ የተግባርና የመስክ ሥራው መጠን አናሳነት ደግሞ እስከ ዶክትሬት የተማሩትን መሐንዲሶች ዕውቀት ብዙም የሚያሳትፍ አይደለም። በእርግጥ የስልጠና፣ የጥናትና የማማከር ሥራዎች እስከ ዶክትሬት የተማሩትን አልፎ አልፎ ሲጋብዝ ይታያል።

አብዛኛው የመስክ ሥራ ሁለገብ በሆኑ መሐንዲሶች ወይም በልምድ ባለሙያዎች እየተሠራ ያለ ከመሆኑ አንፃር ጊዜውን ጠብቆ የሚከሰተው የጥራት ችግር ተጠያቂ የሚያደርገው አካል አያገኝም። ተጠያቂውን ለማግኘትና የትኛው የሥራ ደረጃ ላይ ነገሮች በትክክል ባለመሠራታቸው ችግሩ እንደተከሰተ ነቅሰው የሚያወጡና ቀጣይ መፍትሔን የሚሰጡ ስፔሻላይዝድ ባለሙያዎች በሌሉበት ሁለገብ ባለሙያዎች የሚሰጡት መፍትሔ ሁሉንም በጅምላ ተጠያቂ የሚያደርግ በመሆኑ የሀብት ብክነትን የማይቀንስ፣ የዘርፉን ሙያ የማያሻሽልና በንድፍ ሀሳብ ደረጃ ብዙ የሚነገርለትን የጥራት ጉዳይ በብዥታ የሚያሳይ ሪፖርት ይወጣል።

ለዚህም ነው የመንገድና የድልድይ ጥገና ሥራዎች በወቅቱና በጥራት ለማካሄድ በጥገና ሥራው ላይ ትኩረት ያደረጉ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪ መሐንዲሶችን ማፍራት የሚያስፈልገው።

አሁንም ቢሆን በመንግሥት እጅ ያለ የመንገድ ጥገና ሥራ ቢሮዎችም ሆነ በሥራው ላይ ዘላቂ ተሳትፎ የማድረግ ፍላጎት ያላቸውን ሥራ ተቋራጮችን በተጓዳኝ ማጠናከር ያስፈልጋል። ለዚህም ለጥገና ሥራ አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎችን በተመጣጣኝ መጠን ማቅረብ፣ ቀጣይነት ያለውና በመንገድ ጥገና ላይ ያተኮረ ተከታታይ የተግባር ሥልጠና ለባለሙያዎች መስጠትና የሰለጠኑት ብቻ በስልጠናው መሠረት በሥራ ላይ እንዲሠማሩ ማድረግ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሠራበት ይገባል።

በቅርብ ዓመታት ውስጥ በድልድይ ምርመራና ፍተሻ ሥራ ላይ እንዲሠማሩ የተደረጉ የኢትዮጵያ መንገዶች አገልግሎትና የአማካሪ መሐንዲስ ድርጅቶች ኢንስፔክተሮች በድልድይ ምርመራ ስልጠና ውስጥ ያለፉት ብቻ እንዲሆኑ መደረጉና ይህም ስኬት ማምጣቱ እንደመልካም ማሳያ ሊወሰድ ይችላል።

በእርግጥ ለመንገድ ጥገና ሥራ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን በተሟላ መልኩ ማቅረብ የኢኮኖሚ አቅምን የሚፈታተን እንደሆነ ቢታወቅም በልዩ ልዩ ሁኔታዎች ለምሳሌ ጥራት ለሌለው ሥራ የሚከፈለው ክፍያ ወይም ከጥገና ሥራ ጋር ተመጣጣኝነት ለሌላቸው ከባድ መሣሪያዎች ኪራይ የሚወጣው ወጪ ተደማምሮ የሚባክነውን በጀት መልክ ማስያዝ ይቻላል።

አቅምን ለመገንባት ተግባራዊ ስልጠናን መስጠት የሚችሉ በሥራውና በማሰልጠኑ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች እንዲሁም ለስልጠና የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች በበቂ ሁኔታ አሉ። ጉዳዩ ለአቅም ግንባታ ትኩረት መስጠትና ይህንንም ቢቻል በተቋም ደረጃ በማደራጀት ተከታታይነቱንና ውጤታማነቱን መከታተል ነው። ገበሬውን ከባዶ ለም መሬት ጋር ማፋጠጥ ምርትን እንደማያስገኝ ሁሉ ማደራጀት ሲባልም ባለሙያና መጽሐፍትን አገናኝቶ መተው ሳይሆን ለተግባራዊ ስልጠና የሚያስፈልጉ ጥገና ተኮር የሆኑ መሣሪያዎችን፣ ቁሳቁሶችንና በጀትን በበቂ ሁኔታ ማሟላትን ይጨምራል።

በቀጣዩ ዕትማችን ስለድልድይ ጥገና የምንቃኝ ይሆናል።


**አድራሻ**

Facebook: - Ethiopian Roads Administration Telegram:-ERA ኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር


ከፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የጠፋና የተበላሸ ሠሌዳ ምትክ ለማግኘት

የተሽከርካሪዎች ሠሌዳ የማተምና የማሰራጨት ሥራ ለፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት በውክልና ሰጥቶ ድርጅቱም ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛል። የድርጅቱ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን አምባቸው እንዳስታወቁት፤ የጠፋ ሠሌዳን በማስታወቅ ምትክ ለማውጣት የፖሊስ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፤ ጋዜጣ የታወጀበት (ለጋዜጣ ክፍያ የተፈፀመበት) ሁለት ደረሰኝ ዋና ዋና ኮፒ፤ የፖሊስ ማስረጃው የተሽከርካሪው ፋይል ካለበት ቢሮ ኮፒው ላይ ማረጋገጫ ማህተም የተደረገበትና ተሽከርካሪው ከተመዘገበበት ቢሮ መሸኛ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) ሁሉም ገፅ ፎቶ ኮፒ እና ዋናውን ማቅረብ አለበት፤ የሠሌዳ ክፍያ በዋጋ ተመን መሠረት፤ ምትክ ሠሌዳ እንዲሰራ የሚጠይቀው እና የሚረከበው ባለንብረት ወይም ሕጋዊ ውክልና ያለው ሲሆን የውክልና ማስረጃ እና መታወቂያ ዋናውና ፎቶ ኮፒ ጋር ማቅረብ አለበት።

እንደ አቶ ሰለሞን አባባል፤ ለተበላሸ ሠሌዳ ባለጉዳዮች ማሟላት የሚገባቸው ደግሞ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) ሁሉም ገጽ ዋና እና ፎቶ ኮፒ ማቅረብ አለበት። የሠሌዳ ክፍያ በዋጋው ተመን መሠረት፤ ምትክ ሠሌዳ የሚጠይቀው እና የሚረከበው ባለንብረት ወይም ሕጋዊ ውክልና ያለው ሲሆን የውክልና ማስረጃ እንዲሁም መታወቂያ ዋናውና ፎቶ ኮፒ ጋር ማቅረብ አለበት፤ ሠሌዳ የመረከቢያ የጊዜ ቀጠሮ የሚሰጠው ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ ነው። የተሠራውን ምትክ ሠሌዳ ሲረከቡ የተበላሸው ሠሌዳ መመለስ አለበት፤

የተሽከርካሪ ሠሌዳን ሕትመትና ስርጭት ከትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር በውክልና ተረክቦ ሥራውን በማከናወን ላይ ያለው የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ጉዳይ እናስፈፅማለን



**አቶ ሰለሞን አምባቸው**


በሚል ገንዘብ ከሚጠይቁ ግለሰቦች መጠንቀቅ እንዳለበት አቶ ሰለሞን ያመለክታሉ።

ድርጅቱ የተሽከርካሪ ሠሌዳን በሕጋዊ መንገድ ከክልልና ከአስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮዎች ጋር በመተባበር በመስጠት ላይ መሆኑን ገልፀው፤ የተፈጠረው የሕትመት ስርጭት አከናዋኝ የባለቤትነትን ለውጥ በመጠቀም አንዳንድ ግለሰቦች የሠሌዳ ቁጥር የሚፈልጉ አሽከርካሪዎችን ጉዳይ እናስፈፅማለን በማለት የማታለል ተግባር እየፈፀሙ መሆኑን ይናገራሉ።

እነዚህን ወንጀለኞች ለማጋለጥ ድርጅቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሥራት ላይ መሆኑን በመጥቀስ፤ ሠሌዳ ለሚጠይቁ በክልልና በአስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮዎች አማካኝነት ሕጉን ተከትሎ እየሰጠ በመሆኑ ምንም ዓይነት የጥሬ ዕቃም ሆነ የሕትመት ችግር እንደሌለ ያስረዳሉ።

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራውን ከመረከቡ በፊት በቀን በአማካኝ 3መቶ የሠሌዳ ቁጥሮች ይታተሙ የነበረ ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ የዕረፍት ቀናትን ጨምሮ በምሽት ክፍለ ጊዜ ሕትመትና ስርጭት በመከናወኑ በቀን በአማካኝ ከሦስት ሺህ በላይ የተሽከርካሪ ሰሌዳዎች በመታተም ላይ መሆኑን ይጠቅሳሉ።

ጉዳይ እናስፈፅማለን በማለት ገንዘብ የሚጠይቁ




ግለሰቦች ሲያጋጥሙት ኅብረተሰቡ ለፖሊስ መጠቆም አለበት ያሉት አቶ ሰለሞን፤ ድርጅቱ በተቀላጠፈና በአጭር ጊዜ በሕጋዊ መንገድ የሁሉንም ዓይነት ተሽከርካሪዎች የሠሌዳ ቁጥር እያተመ በማሰራጨት ላይ መሆኑን ይናገራሉ።